# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**አጠር ያለ ስብሰባ ስለ ሪትሪት 2020**

የ2020 ሪትሪትን በተመልከተ አጠር ያለ ስብሰባ ከፕሮግራሙ በኋላ እናደርጋለንና ሁላችንም እንድንሳተፍ በማክበር እንጠይቃለን። ጌታ ይባርካችሁ!

**የ2020 ሪትሪት ፕሮግራም**

- መቼ፡ July 23-25
- የት፡ Green Lake, Wisconsin (same place as last year)
- More information is coming. Please save the dates.

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

“ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**

773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




## “... ነፍሴን መለሳት... ”

(መዝ. 23:3)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**January 26, 2020** | **ጥር 17፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት** ............................ | እህት ሰናይት ከበደ |
| **አምልኮ**.......................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ** ............ | እህት ሰናይት ከበደ |
| **ቃል** ............................... | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| **ማጠቃለያ** ..................... | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"እግዚአብሔር ለእርሱ ሕዝብ ያደርጋችሁ ዘንድ ወድዶአልና እግዚአብሔር ስለ ታላቅ ስሙ ሕዝቡን አይተውም።"

(1ሳሙ. 12:22)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**እግዚአብሔር እረኛዬ ነው -- ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።**

የእግዚአብሔር እረኝነት ከሚገለጥበት መንገድ አንዱ መሪነቱ ነው። እረኛ በጎቹን እንደሚመራቸው ሁሉ ጌታም ይመራናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ስለ እውነተኛ እረኛ ሲናገር በመጀምሪያ እውነተኛ እረኛ መለያው የእርሱ የሆኑት በጎች ድምጹን ለይተው ያውቁታል፤ ደግሞም ይሰሙታል (ዮሐ. 10:3-4)። በጎቹ የእረኛቸውን ድምጽ ከለሌላ ድምጽ ጋር አያምታቱም። ይህ እንግዲህ የሚሆነው በበጎቹና በእረኛው መካከል ተግባቦትና ትውውቅ እንዲሁም በመቀራረብ የተወለደ መታመን ስላለ ነው። እረኛው ለበጎቹ ድምጹን ካሰማ በኋላ በስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል (ቁ. 3)። ከዛም ከፊታቸው ይሄዳል። እንግዲህ ይህ መልካም እረኛ የሚመራው ከፊት በመሄድ ነው እንጂ ከኋላ በመንዳት አይደለም። እረኛችን እግዚአብሔር ከፊት እየሄደ የሚመራ ነው። እኛም ደግሞ ድምጹን ስለምናውቅ እንከተለዋለን።

የእግዚአብሔር መሪነት የሚጀምረው ነፍሳችንን ከማዳን ነው። ዳዊት በዚህ ስፍራ ሁለት ነገሮችን ያነሳል። አንደኛ "ነፍሴን መለሳት" ይላል። ሁለተኛ ደግሞ "ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ" ይላል። መመለስ ያለበት የጠፋ፤ የተቅበዘበዘና ከመንገድ የወጣ ነው። ጌታ ኢየሱስ የመጣው የጠፋውንና የባዘነውን ፍለጋ ነው። ይህንንም በቃሉ "የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና" (ማቴ. 18:11) በማለት ያረጋግጥልናል። እግዚአብሔር የጠፋው ሲገኝ፤ የባዘነው ሲመለስ ደስ ይለዋል። ለዚህም ነው የጠፋነውን ፍለጋ ልጁን የላከው። ስለሆነም እግዚአብሔር እርሱ የሕዝቡ እረኛ መሆኑን ይገልጽና እኔ "የጠፋውንም እፈልጋለሁ የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ የደከመውንም አጸናለሁ" ይላል (ሕዝ. 34:16)። እንግዲህ የእግዚአብሔር መሪነት የተገለጸው በመጀመሪያ የጠፉትውን ነፍሳችንን በመመለስ ነው። ጌታችንም የመጣው ከጥፋት መንገዳችን መልሶ ሊባርከን ነው። ስለዚህም ቃሉ "ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው" (ሐዋ. 3:26)። እረኛችን እግዚአብሔር ነፍሳችንን መልሷታል፤ አድኗታል። ስሙ ለዘላለም የተባረከ ይሁን።

እግዚአብሔር ነፍሳችንን ከጥፋት መልሶ አልተወንም ነገር ግን በጽድቅ መንገድ ደግሞ መርቶናል። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠን ቤዛነትን ብቻ ሳይሆን ጽድቅና ቅድስናንም ሰጥንቶናል። አስቀድም በከንቱነት እየተመላለስን ነበር። ነገር ግን አሁን ቃሉ እንደሚያስተምረን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥበናል፤ ተቀድሰናል፤ ጸድቀናል (1ቆሮ. 6:11)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ ጥበብ፤ ጽድቅ፤ ቅድስናና ቤዛ ሆኖልናል። ስለዚህ እረኛችን ካዳነንና ከቀደሰን፤ በተቀበልነው በዚህ አዲስ ማንነት መመላለስ ግድ ይለናል። ደግሞም አምላካችን ይህንን ቸርነት ያደረገልን ስለ እኛ ማንነት ወይንም በኛ ዘንድ ስለተገኘ በጎነት ሳይሆን "ስለ ስሙ" ነው። የዳነው የክብሩ ምስጋን እንሆን ዘንድ ነው። በፊታችን ባለው ዘመንም እግዚአብሔር ስለ ስሙ ያጸናናል። ቃሉ "እግዚአብሔር ለእርሱ ሕዝብ ያደርጋችሁ ዘንድ ወድዶአልና እግዚአብሔር ስለ ታላቅ ስሙ ሕዝቡን አይተውም" (1ሳሙ. 12:22) እንደሚል እግዚአብሔር የስሙ ክብር ይመሰገን ዘንድ አዳነን ደግሞም በጽድቅ መንገድ መራን።

ወገኖቼ:- ያዳነንና ያጸደቀን ጌታ አሁንም በየእለቱ ይመራናል፤ ከፊታችን ይወጣል። እኛ ግን ሁል ጊዜ ድምጹን መሻት አለብን። ድምጹ ደግሞ በቃሉ በኩል፤ በጸሎት ስፍራችን፤ እንዲሁም በቅዱሳን ሕብረት ወደ እኛ ይፈሳል። አሜን!